ኦገስት 22/ 2008

# ወይ ጣጣ! እውነት ተጋዳሊት ወይስ የቤት እመቤት!

ከአያልነሽ

አጀብ! እግር ሄዶ ሄዶ . . . አሉ

በዚህ ሰሞን የእናት ኢትዮጵያን አዳርና ውሎ ልጎበኝ ወደ ድረ ገጾች ዘንድ ጎራ ስል፣ ድንገት የወያኔ/ህወኃት ንብረት የሆነው አይጋ በጥፊ ብሎ አጠናገረኝ። እንደ አገሬ ባህል ቢሆን ኖሮ ምች ሳጠናገረው ድንገተኛ የምቹን መድኃኒት ፍለጋ ሰንት ቦታ ላይ በተወጣና በተወረደ ነበር። ከደደቢት በፈለሰው ምች ተመትቸ "እኔን" የሚለኝ ባላገኝም አይጋ ላይ አወዳደቄ ግን ድንገትና ሳላሰብ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም፤ ይባስ ብሎ ከወደቅሁበት ቀና ብዬ አይጋን ሰቃኝ ደግሞ " ኢንተርቪው ከፈርሰት ሌዲ አዜብ መሰፍን ጋር" ይልና የተጋዳሊት አዜብ ጎላ ምስልም አብሮ ተለጥፏል። ሶስቴ አማተብኩና ሰፈራ ሰቸር ዘልዬ ይህንን መጠይቅ ከፈትኩ። መቼስ የእነ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ኢትዮጵያ ዛሬ በእነ አዜብ ጎላ እጅ ወድቃለችና የምዬ ኢትዮጵያን አዳርና ውሎ በየጊዜው መከታተልና ማዳመጥ ለነገ የማንለው፣ ጊዜ የማይሰጥን ጉዳያችን በመሆኑ የኢትዮጵያዊያኖች በሞላ ግዴታና ኃላፊነት መሆኑ አልቀረም። እዬዬም ሲደላ ነው ተብሎ የለ። ዛሬ እናት ኢትዮጵያ በወያኔ አገዛዝ ሥር እግር ከወርች ታስራ እየማቀቀች በምትገኝበት ሁኔታ፣ የጎላ ልጅ አዜብ እነደምትለውና እንደነገረችን አይደለችም ኢትዮጵያችን። የዛሬዋ ኢትዮጵያ ህጻናት የሚቧርቁባትና በደስታ የሚፈነጥዙባት ሳትሆን ይልቁንም በግልባጩ እይታ ሰንቃኛት ሚሊዮኖች በ"አረንጓዴው" ረሃብ የሚረግፉባትና ሕጻናት የሲቃ ለቅሶ እያሰሙ ልብ የሚሰብረውን ዋይታቸውን የሚያሰሙባት ሲኦል ናት። ይህንን እውነታ በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ የዜና ምንጮች ሳይቀሩ በፎቶ ግራፍ አሰደግፈው እየዘገቡት የሚገኘውን ሐቅ በዘረፋት ሀብቷ ለሚምነሸነሹት ዘመነኞች ለነ አዜብ ጎላ ግን ዛሬም ድብቅ ነው። እስቲ ወደ ቁም ነገሬ ከማለፌ በፊት እግረ መንገዴን አንድ ያሰደነቀኝን ትዝብቴን ላካፍላችሁ።

የኢትዮጵያን ፈርስት ባለቤት የሆነው ጋዜጠኛ አዜብ ጎላን ከልክ በላይ ሄዶ ያለ የሌለውን ሙገሳ አጎናጽፎና እንዲህ ተጨነቆና ተጠቦ ከስሟ በፊት "ቀዳማይ እመቤት" በማለት ሊጠራት የሞከረው ጋዜጠኛ (ልብ ብሎት ከሆነ) ከጤፍ ፍሬ እጅግ አሳንሶ በሚያሳይ መንገድ ይህንን አጓጉል የሆነ ከንቱ ውዳሴን እንዲህ በማለት አጣጥላዋለች።

"ቀዳማይ እመቤት ማለት የእገሌ ሚስት ነሽ ለማለት ነው፣ ይሄ ደግሞ ማንነቴን ስለማይገልጸው አባባሉ ግምት ሰጥቶኝ አያውቅም፤ አላስብበትምም እና ለእኔ ይህ አጠራር ትርጉም አይሰጠኝም"

በማለት ጋዜጠኛውን ጥፍሩ ውስጥ እንዲገባ አድርጋዋለች። ቅሌት። ወይዘሮ/ ወይዘሪት የተባሉት አባባሎቻችን ምን አጠፉና ነው ይሄ ሁሉ ጭንቀት ጃል። ጋዜጠኛ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ቂ ! አቤት መጥኔ

ሳይቸግር ጨው ብድር አሉ። አጃኢብ! እንዲህ እንዲህ ዓይነት ኃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች ያለ የሌለን ከንቱ ውዳሴ በማዥጎድጎድ ይካኑና ሰውን ከሰውነት እንዲወጣ ያደርጉታል። ባለፈው ሥርዓትም እንዲሁ ደካማ የሆኑ ግለሰቦች ውዳሴ ከንቱን እንግሥው የደርጉ ዋና ቁንጮ ለነበረው መንግሥቱ ኃ/ማርያምን አሳብደው አንድ ትውልድ ተቀጥፏል። የቅርብ ትዝታዎቻችን መለስ ብለን ስንቃኝ "ቪቫ መንግሥቱ ኃ/ማርያም! ከጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጋር ወደፊት! ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!" የሚሉትና የመሳሰሉትን የቃላት ሰይፎች ያስታውሷል። ሰውን ከሰውነት የሚያወጣ የግብዞች ልክ የሌለው የከንቱ ውዳሴ ስጦታ። አዜብ ጎላን እንግዳው አድርጎ ያቀረባት የኢትዮጵያን ፈርስት ጋዜጠኛ ደግሞ እንዲሁ ኢትዮጵያን እያፈራረሰ ያለውን የወያኔ ቡድንና አገዛዝ ቁንጮ ለሆነችው ሴት ይሄን የመሰለ አስገማች ውዳሴን ማንቆርቆር እንኳን ለታዛቢ ቀርቶ ይሉኝታ ላለመደባትና ላላሳደጋት አዜብ ጎላም ጭምር ውዳሴው አስደምሟታል። አጀብ! የጉድ አገር። ውድ አንባቢዎች! ሌላም ገጠመኝ ልጨምራችሁ። እስቲ በጥሞና ተከታተሉት አባካችሁ! ገጠመኙ እንዲህ ይነበባል።

ጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ የአቶ ታምራት ላይኔን "ኃጢያት" ዘርዝረው "ከም/ጠ/ ሚኒስትርነትና ከመከላከያ ሚኒስትርነቱ እንዲነሳ ወስኛለሁ" በማለት ለምክር ቤት ሲናገሩ የም/ቤቱ አፈ ጉባዔ ዳዊት ዮሐንስ ፈጠን ብለው "የአቶ መለስን ውሳኔ የምትደግፉ የምትቃወሙ" በማለት የምክር ቤቱን አባላት ድምፅ አሰጡ። በህገ መንግሥቱ እንደሠፈረው ም/ጠ/ሚኒስተሩንም ሆነ ሚንስትሮችን ከሥልጣን የማንሣቱ መብት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያልተሰጠና ለጠ/ሚኒስትሩ የተተወ ሆኖ ሣለ አቶ ዳዊት ዮሐንስ ከሕገ መንግሥቱ የወጣ አሠራር ሲከተሉ፣ ሁሉም የም/ቤት አባል እጁን በማውጣት ለሕገ መንግሥቱ ባዕድ መሆኑን አረጋግጧል። ከዚያ ሁሉ የም/ቤት አባል የአቶ ዳዊት ዮሐንስ አካሄድ ሕገ-ወጥ ነው ብለው ያረሟቸው ራሳቸው ጠ/ሚኒስትር መለስ ብቻ ነበሩ" ይላል

(ኢትኦጵ ቅፅ 3 ቁ.ጥር 026 ሀምሌ 1993ዓ.ም)

አያችሁ! ጨሉሌው ለገሠ ዜናዊ አስቀድሞ እንዲቀል ያስደረገውን ዳዊት ዮሐንስ፣ ተመልሶ አራሚና አስተካካይ ሆኖ ቀረበና ዳዊት ዮሐንስን የለመደበትን ቅሌት አከናንቦ ተጠቅልሎ እንዲተኛ አድርጎታል። ወይ መቸገር! ”ሳይቸግር ጨው ብድር” የሚያሰኘው እንዲህ ዓይነቱ ቅሌት ነው። አያድርስ! ነውየሚባለው።

በጁ! የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ! ወደ ቁም ነገሬ ልመልሳችሁ፤ የኢትዮጵያን ፊርስት ጋዜጠኛ እንግዳ የሆነችው ተጋዳሊት አዜብ ጎላ ቆይታ ስላደረገችበት ጉዳይ እንዳልወሰዳችሁ የአዜብ ጎላ ጨዋታ አንቶ ፈንቶ ሆነብኝና ቁም ነገር ባጣበት እሳት ካየው ምን ለየው እንደተባለው ከባለቤቷ ከለገሠ ዜናዊ የተለየ ነገር ሳታወራ ሄደች። ነገር ግን የተለመደው ተጨፈኑ ላሞኛችሁ ዲስኩር በለመድነው አባባል "በኢትዮጵያ ሠላም፣ ልማትና ዕድገት በከፍተኛ ፍጥነት እየተተኮሰ ነው፤ ነገር ግን እርግጥ ነው ይሄንን የጀመርነውን ልማታችንና እድገታችንን ለማሳካት ከዚህ በተሻለ ቅልጥፍና እንዳናስኬደው ማነቆዎች ገጥመውናል፤ ትልቁ እንቅፋትና ማነቆ ደግሞ መጀመሪያውኑ ከደርግ የተረከብናት ኢትዮጵያ ደሃና ባዶ የነበረች መሆኗ ነው" አለችን እመት አዜብ። ወይ ዕድሜ ዘልዛላው! ጀሮ መዝጊያ የለው ጎበዝ! ምን የሚሉት አማርኛ ነው? እንዴት እንዴት ነው ጨዋታሽ አዜብ? በባዶ እግራቸው ያለጫማ የገቡት የደደቢት ዘመነኞችን ዓመት ሳይሆናቸውና ሳይሞላቸው ሚሊየነር ያደረገች፤ ባለሃብትና ባለጸጋ አድርጋ ውበትን ላላበሰች፣ ያ የመከራና የስቃይ ዘመንን አራግፋ ያስጌጠች ቅድስት ኢትዮጵያ እንዴት ዛሬ በአዜብ ጎላ ድሃ ናት ተብላ ትታማ? ኧረ የሰው ያለህ! ”አፍን ይበሉበታል እንጅ ከፋ አይናገሩበትም” የተባለውን ብሂል የጎላ ልጅ አዜብ ባትሰሚ ይሆናል። ይቅር ይበልሽ እቱ።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን!